# በ2010 በጀት ዓመት በጀት ላይ ወጪን ለመቀነስ የተዘጋጀ የአዘገጃጀትና የአቀራረብ መመሪያ

ገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር

ሐምሌ/2009

# በ2010 በጀት ዓመት በፌዴራል መንግስት ባለበጀት መ/ቤቶች የሚደረጉ የወጪ ቅነሳ ስልቶች

## I. መግቢያ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት ግንቦት 25 ቀን 2009 ዓ.ም የፌዴራል መንግስትን የ2010 በጀት ዓመት የበጀት ሰነዶችን በመገምገም ባስተላለፈው ውሳኔ መሰረት የመንግስት በጀት ውጤታማ እና ወጪ ቆጣቢ በሆነ መልኩ እንዲተገበር የገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር በየመ/ቤቱ በተመደበው በጀት ላይ "ወጪ የሚቀነስበትን አማራጭ አይቶ ለእያንዳንዱ መ/ቤት" ማሳወቅ እንዳለበት ወስኗል፡፡ በተጨማሪም "እያንዳንዱ መ/ቤት የገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር ወጪ ቅነሳ ላይ በሚሰጠው አቅጣጫ መሰረት የበጀት ሽግሽግ የሚያደርግበት አግባብ ሊያቀርብ እንደሚገባ" ካቢኔው ወስኗል፡፡ በዚሁ መሰረት በፀደቀው የ2010 በጀት ላይ የወጪ ቅነሳ ለማድረግ የሚያስችሉ የወጪ አይነቶችን በመለየት የሚከተለውን አሰራር በመ/ቤቶች በኩል እንዲተገበር ይህንን አጠቃላይ መመሪያ ማስተላለፍ አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ ስለሆነም እያንዳንዱ አስፈጻሚ መ/ቤት ከዚህ በታች በተቀመጡት አቅጣጫዎች እና ከዚህ ውጭም በመ/ቤቱ በኩል ሊታዩ የሚችሉ የወጪ አይነቶቹን በመፈተሽ ሊቀነስ የሚችለውን በጀት ለገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር ማሳወቅ አለበት፡፡

## II. የፕሮግራም በጀትን መርህ በጥብቅ መከተል

የፕሮግራም በጀት ስርዓት በጀትን ከውጤት ጋር በማስተሳሰር ውጤታማነትን እና የወጪ ቁጠባን የሚያረጋግጥ ነው፡፡ የፕሮግራም በጀት የፕሮግራም ውጤቶች እና ዋና ተግባራትን በግልጽ በመቅረጽ፣ የሚያስፈልጋቸውን ወጪንም በትክክል በማስላት በጥብቅ ዲሲፒሊን ተግባራዊ ከተደረገ የበጀት ውጤታማነት እና ቁጠባን ማረጋገጥ ያስችላል፡፡ ስለሆነም ባለበጀት መ/ቤቶች ከ2010 በጀታቸው የሚጠበቅባቸው ቀዳሚው ጉዳይ ወጪን ለመቀነስ ለፕሮግራም ውጤቶች እና ዋና ተግባራት የመደቡት በጀት ቁጠባን መሰረት ያደረገ መሆኑን መፈተሽ ነው፡፡ ከዚህ በመነሳት የታቀዱት ዓላማዎች፣ ግቦችና ውጤቶች አንደተጠበቁ ሆነው የሚጠይቁት ወጪ የሚቀንስበት ሁኔታ ማየት ያስፈልጋል፡፡

ባለበጀት መ/ቤቶች ቀጥሎ ማድረግ የሚጠበቅባቸው የጸደቀውንና በኃላም የወጪ ሽግሽግ ተደርጎባቸው የሚያዘውን የፕሮግራም በጀት በጥብቅ የፊሲካል ዲሲፕሊን ማስተዳደር ነው፡፡ በአሁኑ ወቅት መንግስትን ለከፍተኛ ወጪ እየዳረገ ያለው መ/ቤቶች የፕሮግራም ዓመታዊ

ግብና ውጤትን መሰረት ያላደረገ የበጀት ዝውውር እና የተጨማሪ በጀት ጥያቄ ነው፡፡ የፕሮግራም በጀት ለእያንዳንዱ ውጤት የሚያስፈልገው በጀት ተሰልቶ የሚያዝ በመሆኑ ዲሲፕሊኑን ያልጠበቀ የበጀት ዝውውርና የተጨማሪ በጀት ጥያቄ አይጠበቅም፡፡ ስለሆነም የበጀት ቁጠባ ለማረጋገጥ ባለበጀት መ/ቤቶች በፕሮግራም ውጤት ላይ ተመስርቶ የጸደቀውን በጀት በጥብቅ ዲስፕሊን ማስተዳደር ይጠበቅባቸዋል፡፡

## III. የመደበኛ ወጪን በተመለከተ፡-

1. የትርፍ ሰዓት ክፍያን በተመለከተ፡- በመንግስት ባለበጀት መ/ቤቶች የትርፍ ሰዓት ክፍያ ስራ ላይ የሚውለው በፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ሀብት ልማት ሚኒስቴር ሲፈቀድ ብቻ ነው፡፡ ዩኒቨርሲቲዎችን በተመለከተ ግን መምህራን ከጫና በላይ /Over Load/ ሊያስተምሩ የሚችሉት የመምህራን እጥረት በሚኖርበት ጊዜ ቢሆንም አንዳንድ ዩኒቨርሲቲዎች መምህራንን ከመቅጠር ይልቅ ከጫና በላይ ለማስተማር በዕቅዳቸው አካተው የሚንቀሳንቀሱ በመሆናቸው በትምህርት ጥራት ላይ ተፅዕኖ እያሳደረ በመሆኑ እና በመንግስት ላይ ተጨማሪ ወጪ እያስከተለ መሆኑ ታውቆ አስፈላጊው ማስተካከያ መደረግ አለበት፡፡

2. የቢሮ አላቂ ዕቃዎችን በተመለከተ፡- በየመ/ቤቱ የተዘረጋውን የኢንፎርሜሽን ሲስተም በመጠቀም የወረቀት፣ የቶነር እና የመሳሰሉትን ግዥዎች በመቀነስ ወረቀት አልባ አሰራርን መተግበር ያስፈልጋል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ እንደ ማስታወሻ ደብተር፣ ስክሪፕቶ እና የመሳሰሉትን እንደየስራው ሁኔታ የሚያስፈልገውን መጠን በመወሰን በእነዚህ ወጪዎች ላይ ቅናሽ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡

3. ሕትመትን በተመለከተ፡- በየመ/ቤቱ የሚደረጉ የሕትመት ውጤቶች አስፈላጊነታቸው በአግባቡ በመፈተሽ እና የኢንፎርሜሽን ሲስተምን በመጠቀም ወጪ መቀነስ ያስፈልጋል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ የመ/ቤቱ ተልዕኮ ለመወጣት በማያስፈልጉ ወጪዎች ማለትም የቀን መቁጠሪያ ካላንደር፣ አጀንዳ፣ መጽሔት፣ የደስታ መግለጫ ካርድ በማስቀረት ወጪ መቀነስ ያስፈልጋል፡፡ እንዲሁም ለስራ አስፈላጊ የሆኑ ሕትመቶች ከስራው ጋር የተጣጣሙ መሆናቸውን እያረጋገጡ ግዥ መፈጸም ይገባል፡፡

4. ነዳጅና ቅባትን በተመለከተ፡- የነዳጅ አጠቃቀምን እና ቁጥጥርን በማጠናከር ለመንግስት ስራ ብቻ መዋሉን ማረጋገጥ ያስፈልጋል፡፡ የተሽከርካሪ ስምሪት በማቀናጀት እና ቁጥጥር በማድረግ እንዲሁም በመኪና የነዳጅ አጠቃቀም ስታንዳርድ /ነዳጅ በኪ.ሜ እንደ መኪናው አይነት/ በመወሰን የነዳጅ ፍጆታ የሚቀንስበትን አካሄድ መፈተሽ ያስፈልጋል፡፡

5. የተሽከርካሪ ጥገናን በተመለከተ፡- የተሽከርካሪ ጥገና መከናወን ያለበት እንደማንኛውም የግዥ አገልግሎት በጨረታ መከናወን አለበት፡፡ በመሆኑም ከዚህ በፊት በትላልቅ የተሽከርካሪ አስመጪ ኩባንያዎች በቀጥታ ስምምነት ጥገና በማድረግ የሚወጣውን ወጪ መቀነስ ይቻላል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ለመንግስት ንብረት አያያዝ ተገቢውን ትኩረት መስጠት ያስፈልጋል፡፡ በረጅም አገልግሎት ወይም በብልሽት ተጠግነውም የነዳጅ ፍጆታቸው ከፍተኛ የሆኑ እና አገልግሎት የማይሰጡ ተሽከርካሪዎችን እንዲወገዱ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡

6. የጽዳት አላቂ ዕቃዎችን በተመለከተ፡- በየመ/ቤቱ ለጽዳት አገልግሎት ለሰራተኞች የሚሰጡ ዕቃዎችን ለምሳሌ ሶፍት እና ሳሙና መጠን የሚቀነስበትን ሁኔታ ማመቻቸት እንዲሁም የተሽከርካሪ ሽቶ፣ ኤርፍሬሽነር እና የመሳሰሉት ግዥ በቁጠባና አስፈላጊነቱ አየተረገገጠ ብቻ መከናወን አለበት፡፡ በተጨማሪም በጽዳት አላቂ እቃዎች አጠቃቀም ላይም ቁጥጥር ማድረግ ያስፈልጋል፡፡

7. የመስተንግዶ ወጪን በተመለከተ፡- በየመ/ቤቱ ለሚደረጉ የመስተንግዶ ወጪዎች በአግባቡ በመፈተሽ አላስፈላጊ ወጪዎችን መቀነስ ያስፈልጋል፡፡ ከዚህ ጋር ተያይዞ በየመ/ቤቱ ለሚደረጉ ስብሰባዎች፣ ወርክሾፖች እና ሴሚናሮች እንደ ሻይ፣ ቡና እና ውሃ ከመሳሰሉት ወጪዎች በስተቀር ሌላ ግብዣ ማድረግ አይቻልም፡፡ በተጨማሪም ከባለድርሻ አካላት ጋር ለሚካሄዱ ስብሰባዎች እና ክብረ ባዕሎች ለተሳታፊዎች የሚሰጡ ቦርሳ፣ ቲሸርት፣ ካኒቴራ፣ ኮፍያ፣ ሻርፕ እና የተለያዩ የሀገር ባህል ልብሶች መግዛት አይቻልም፡፡ በተቻለ መጠን ስብሰባዎች በየተቋማቱ መሰብሰቢያ አዳራሾች በማካሄድ ለሆቴሎች የሚወጣውን ወጪ ማስቀረት ይቻላል፡፡

8. የማስታወቂያ ወጪን በተመለከተ፡- ባለበጀት መ/ቤቶች ለህዝብ ጥቅም መተላለፍ ካለባቸው መልዕክቶች በስተቀር ራሳቸውን በብዙሃን መገናኛ ዘዴዎች ማስተዋወቅ እና

ሌሎች ድርጅቶችን ወይም ባዕላትን ስፖንሰር ማድረግ አይቻልም። የመንግስት በጀትን በድጋፍ መልክ ለሌላ ማስተላለፍ አይቻልም።

9. የተሽከርካሪ ኪራይ ወጪን በተመለከተ፡- በባለበጀት መ/ቤቶች አቅም በፈቀደ መጠን በማዕከል ተሽከርካሪ ግዥ ተከናውኖ ተሽከርካሪ የሚመደብ በመሆኑ ለተሽከርካሪ ኪራይ በበጀት ካልተፈቀደ በስተቀር ወጪ መደረግ የለበትም።

10. የስልክ ወጪን በተመለከተ፡- ከመንግስት ከፍተኛ ኃላፊዎች እና የሌሎች ተቋም ኃላፊዎች በስተቀር ለሞባይል ካርድ መግዣ ወጪ ማድረግ አይቻልም። ከዚህ በተጨማሪ ለመካከለኛ አመራሮች እና ሰራተኞች ለቀጥታ ስልክ እንደስራው ጸባይ ተመጣጣኝ የሆነ የስልክ ወጪ በተመን በመመደብ ወጪ መቀነስ የሚያስፈልግ ሲሆን ከተመን በላይ እንዳይጠቀሙ ቁጥጥር ማድረግ ያስፈልጋል።

11. የውጭ ሀገር ጉዞን በተመለከተ፡- የሚኒስቴር መ/ቤቶች በስራቸው ያሉትን የተጠሪ መ/ቤቶች ኃላፊዎች ጭምር የውጭ ሀገር ጉዞ ፕሮግራም ማለትም የፕሮግራም ዓላማ፣ የታሳታፊ ብዛት፣ የቆይታ ጊዜ እና ወጪን የሚያሳይ የውጭ ጉዞ ፕሮግራም በማዘጋጀት ለጠቅላይ ሚኒስትር ጽ/ቤት ቀርቦ ሲፈቀድ ተግባራዊ ይሆናል። ከዚህ ውጭ በመካከለኛ አመራርና ባለሙያ ደረጃ የሚደረጉ የውጭ ሀገር ጉዞዎች የውጭ ጉዞው ሊያስገኝ የሚችለውን ጠቀሜታ በአግባቡ በመገምገም ለትራንስፖርት እና ለውሎ አበል የሚወጣውን ወጪ መቀነስ ያስፈልጋል።

12. የሀገር ውስጥ ጉዞን በተመለከተ፡- በየመ/ቤቱ የሚደረጉ የመስክ ስራዎች በተጨባጭ የመስክ ጉዞው አስፈላጊነትን በመገምገም በቅድሚያ የመስክ ዝርዝር ፕሮግራም በማዘጋጀት እና የቆይታ ጊዜ በመወሰን ወጪ ቆጣቢ እና ውጤታማ በሆነ መንገድ በማከናወን ለትራንስፖርት እና ለውሎ አበል የሚወጣውን ወጪ መቀነስ ያስፈልጋል።

13. ስልጠና እና ስብሰባን በተመለከተ፡- ከዚህ በፊት የተደረጉ ስልጠናዎች እና ስብሰባዎች ያስገኙትን ውጤት በመገምገም አስፈላጊ የሆኑ ስልጠናዎችን እና ስብሰባዎችን በመለየት ስልጠናው እና ስብሰባውን በማካሄድ ወጪን መቀነስ ያስፈልጋል። በተለያዩ ጊዜ የሚደረጉ ስልጠናዎች እና ስብሰባዎች በአነስተኛ ወጪ ማለትም ሻይ፣ ቡና እና

ውሃ የመሳሰሉትን በማቅረብ ብቻ እንዲከናወን ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ ከዚህ ውጭ በአዲስ አበባ ስብሰባ ሲካሄድ በህግ ከተፈቀደው ውጭ ወጪ መፈጸም ክልክል ነው፡፡

14. የቢሮ ኪራይን በተመለከተ፡- ባለበጀት መ/ቤቶች አዲስ ቢሮ መከራየት አይችሉም፡፡ ተከራይተው ከፍተኛ ወጪ እየከፈሉ ያሉ መ/ቤቶችም ወጪው የሚቀንስበትን መንገድ መፈተሽ ይገባቸዋል፡፡

15. የሙያ አገልግሎት ክፍያን በተመለከተ፡- መ/ቤቶች የጥበቃ፣ የጽዳት እና የመሳሰሉት አገልግሎቶች ለማግኘት ከውጭ አቅራቢዎች ጋር ውለታ ሲፈጽሙ /Outsource/ የተመደበላቸውን በጀት ግምት ውስጥ በማስገባት በአነስተኛ ወጪ መሆኑን በማረጋገጥ መሆን ይገባዋል፡፡

16. ቋሚ ዕቃን በተመለከተ፡- በየመ/ቤቱ ያሉ ቋሚ ዕቃዎችን በአግባቡ ጥቅም ላይ እንዲውሉ በማድረግ እና ጥገና የሚያስፈልጋቸውን በማስጠገን የአገልግሎት ጊዜያቸውን በማራዘም የቋሚ ዕቃን ግዥ ወጪ መቀነስ ያስፈልጋል፡፡ ከአዲስ ሰራተኛ ቅጥር ጋር ተያይዞ የሚያስፈልግ ቋሚ ዕቃ ግዥ ካልሆነ በስተቀር የቋሚ ዕቃ ግዥ ማከናወን አይቻልም፡፡ የሚገዙ ቋሚ ዕቃዎችም በአነስተኛ ወጪ ከአገር ውስጥ እንዲከናወን መደረግ ይኖርበታል፡፡

17. ድጋፍና ስጦታን በተመለከተ፡- ባለበጀት መ/ቤቶች /ከዩኒቨርሲቲዎች ከክረምት ተከታታይ ተማሪዎች እና በዩኒቨርሲቲዎች ከሚማሩ አካል ጉዳተኞች በስተቀር/ ለማንኛውም ድርጅት ሆነ ግለሰብ የገንዘብ ድጋፍ ወይም ስጦታ መስጠት አይችሉም፡፡

18. የውሃ እና የኤሌክትሪክ ወጪዎችን በተመለከተ፡- ባለበጀት መ/ቤቶች ለእነዚህ አገልግሎቶች የሚያወጡትን ወጪ የሚቀንስበትን መንገድ መፈተሽ ያስፈልጋል፡፡

19. ንብረት አስተዳደርን በተመለከተ፡- የመንግስት ንብረት በአግባቡ ስራ ላይ እንዲውል በጥንቃቄ መያዝና ወጪ በሚቀንስበት መልኩ ማስተዳደር እንዲሁም ያለጥቅም የተከማቹ ንብረቶችን ማስወገድ ያስፈልጋል፡፡

## IV. የካፒታል ወጪን በተመለከተ

መንግስትን ለከፍተኛ ወጪ እየዳረገ ያለው አንዱ ጉዳይ የፕሮጀክቶች አዘገጃጀትና አስተዳደር ነው። ፕሮጀክቶች ያለበቂና ባልተሟላ ጥናትና ዲዛይን እንደዚሁም ተገቢው ቅድመ ዝግጅት ሳይደረግ መጀመር፣ የኮንስትራክሽን አገልግሎት ግዥ ወጪ ቆጣቢ አለመሆን እና ጠንካራ የኮንትራት አስተዳደር አለመኖር መንግስትን ለከፍተኛ ወጪ እየዳረጉ ናቸው። በዚህም ምክንያት ፕሮጀክቶች በታቀደላቸው የፕሮጀክት ጠቅላላ ወጪ፣ ጊዜ፣ ጥራትና መጠን እየተጠናቀቁ አይደሉም። ስለሆነም የሚተገበሩ ፕሮጀክቶች በአግባቡ በማቀድ በታቀደላቸው የጊዜና የጥራት ደረጃ እንዲጠናቀቁ ማድረግ ቅድሚያ የሚሰጠውና ወጪ የሚቀነስበት ዘዴ መሆኑ ታውቆ ሊሰራበት ይገባል።

1. ፕሮጀክቶች በታቀደው ጊዜ፣ ወጪ እና ጥራት እንዲከናወኑ የፕሮጀክት ማኔጅመንት ስርዓትን በማጠናከር አስፈጻሚ መ/ቤቱ ከስራው ተቋራጩ እና ከአማካሪ ድርጅቱ ጋር በጋራ የስራ አፈጻጸሙን በየጊዜው በመገምገም ፕሮጀክቱ ተጨማሪ ወጪ እና ጊዜ እንዳያስከትል መደረግ አለበት።

2. በበጀት አዋጁ ከጸደቀው ፕሮጀክት ውጭ ፕሮጀክቶችን ማካሄድ አይቻልም።

3. የፕሮጀክቶች የቅድመ ዝግጅት ስራዎችን ማለትም የቦታ ርክክብ፣ የዲዛይን ስራ፣ የጥናት ስራዎችን አስቀድሞ በመስራት በፕሮጀክቱ ትግበራ ሊያጋጥሙ የሚችሉ ችግሮችን ከወዲሁ በመፍታት ፕሮጀክቶችን ውጤታማ እና ወጪ ቆጣቢ በሆነ መልኩ መተግበር ያስፈልጋል።

4. እነዚህን መሰረት በማድረግ አዲስ በሚጀመሩና በመካሄድ ላይ ባሉ ፕሮጀክቶች ወጪ የሚቀነስበት መንገድ በዝርዝር በመፈተሽ ለ2010 የተያዘውን በጀት ወጪ በመቆጠብ መጠቀም ያስፈልጋል።